**የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ መመሪያ**

**Apiculture Resources Development and Protection Directive**

**መመሪያ ቁጥር 1028/2017 ዓ.ም**

**Directive No.1028/2024**

**የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ መመሪያ**

**Apiculture Resources Development and Protection Directive**

የግብርና ሚኒስቴር በንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2002 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

The Ministry of Agriculture has issued this directive pursuant to sub-article 2 of Article 9 of the Apiculture Resources Development and Protection Proclamation No.660/2009.

## ክፍል አንድ
## ድንጋጌዎች ጠቅላላ

## Part One
## General Provisions

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1028/2017 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**1. Short Title**

This Directive may be cited as the **"Apiculture Resources Development and Protection Directive No. 1028/2024."**

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሃረጉ አግባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

**2. Definition**

In this directive, unless the context requires otherwise:

1)**"አዋጅ"** ማለት የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2002 ነው፡፡

2) **"ደንብ"** ማለት የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 372/2008 ነው፡፡

3) **"አግባብ ያለው አካል"** ማለት የግብርና ሚኒስቴር ወይም በክልል ግብርና የሚመለከተው የመንግስት ተቋም ነው፡፡

4) **"ተቆጣጣሪው አካል"** ማለት የኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን ወይም የክልል ተቆጣጣሪ አካል ነው፡፡

5) **"አፅቂ ነፍሳት"** ማለት የጀርባ አጥንት የሌላቸው ነፍሳት ማለት ነው፡፡

6) **"በዘመናዊ መንገድ ማነብ"** ማለት ባለፍሬም ወይም የሽግግር ወይም ባህላዊ ቀፎዎችን እና ዘመናዊ ወይም የተሻሻሉ የማናቢያ ቁሳቁሶችንና ግብዓቶችን በመጠቀም ለንቦች የሚያስፈልጉ መጠለያ በማዘጋጀት፣ የንብ ቀሰም ዕፅዋቶችን በማልማት ወይም በመንከባከብ ወይም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ መኖን በመመገብ የሚከናወን የንብ ዕርባታ ስራ ነው፡፡

7) **"ዘረ-መል"** ማለት ተወራራሽ ባህሪያትን የሚያስተላልፍ በማንኛውም ሕይወት ያለው ነገር ውስጥ የሚገኝ የዘር ውርስ ክፍል ነው፡፡

8) **"ንፅህና"** ማለት የንብ እርባታ ቦታን፣

1) ''Proclamation''means Apiculture Resources Development and ProtectionProclamation No.660/2009.

2) **''Regulation''** means the Apiculture Resources Development and Protection Council of Ministers Regulation No. 372/2016.

3) "**Appropriate Body**" means the Ministry of Agriculture or the government institution concerned with regional agriculture.

4) "**Regulatory Body"** means the Ethiopian Agricultural Authority or Regional regulatory body.

5) **"Insects"** means any of a group of small and often winged invertebrate animals.

6) **''Modern Beekeeping''** means keeping honeybee colonies by using frame or transition hives or traditional hives with modern or improved accessories and inputs and by providing shelter, cultivating or managing bee flora, and if necessary, by providing other supplementary feeds.

7) **"Gene"** means hereditary unit found in living things that transfer characters from parents.

8) **''Hygiene''** means keeping apiary sites, equipment, bee and bee products

የማነቢያ ቁሳቁስን፣የንብና የንብ ዉጤቶች ማቀነባበሪያ፣ማከማቻና ማጓጓዣን ከኬሚካል፣ ከባዕድ ሽታ እና ከንብ ጠላት ነፃ ማድረግ ነው፡፡

9) **"ባዕድ ነገር"** ማለት የንብ ውጤቶችን ተፈጥሮአዊ ባህሪይና ይዘት የሚለውጥ ማንኛውም ነገር ነው፡፡

10) **"የንግድ አዋጭነት ዕቅድ"** ማለት በንብ ሀብት ልማት ወይም የንብ ውጤቶች ንግድ ወይም የቅድመና የድህረ ምርት ንብ ማነቢያ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ማምረትና ንግድ ስራ ላይ የሚሰማራ ሰው የሚያቀርበው ዝርዝር የስራ እቅድ ነው፡፡

11) በአዋጅ እና በደንብ የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት አላቸው፡-

**ክፍል ሁለት**

**የአናቢዎች ምዝገባ እና የማነቢያ ሥፍራ አወሳሰን**

3. <u>የአናቢዎች ምዝገባ</u>

1) ማንኛውም በከተማም ሆነ በገጠር የሚኖር አናቢ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ህብረ-ንቦችን በግዢ፣በውደት፣በስጦታም ሆነ በማራባት ያገኘውን ህብረ-ንብ በዘመናዊ መንገድ የሚያነብ ከሆነ በቀፎው ውስጥ ህብረ-ንብ ካስገባበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ አግባብ ያለው አካል በሚገኝበት ወረዳ ወይም ቀበሌ ጽ/ቤት ማስመዝገብ አለበት፡፡

processing, storage, and conveyance free from chemicals, foreign odor, and bee enemies.

9) **"Foreign Thing"** means anything that changes the natural behavior and contents of bee products.

10) **"Business plan"** is a detailed work plan prepared by a person engaged in honeybee resource development, bee product business, or pre and post-harvest beekeeping equipment production and business.

11) Definitions given in the proclamation and regulation shall also apply to this directive

**Part Two**

**Registration of Beekeepers and Apiary Site Determination**

**3. <u>Registration of Beekeepers</u>**

1) Any urban or rural beekeeper who keeps honeybees that are obtained through purchase, gift, and multiplication or swarming in a modern way shall register the honeybee colonies by the appropriate body at woreda or kebele office within 3 months from the date he places bee colony in the beehive.

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ሀብረ-ንቡን ያስመዘገበ አናቢ አዲስ ሀብረ-ንብ በግዢ ወይም በስጦታ ወይም አባዝቶ ወይም በዑደት ምክንያት የተገኘውን ሀብረ-ንብ ወደ ቀፎ ሲያስገባ የተገኘውን አዲስ ሀብረ-ንብ ካስገባበት ቀን ጀምሮ በ 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ አግባብ ያለው አካል ማስመዝገብ አለበት፡፡

3) አግባብ ያለው አካል አገራዊ መረጃ ለመያዝ ያስችለው ዘንድ ለሀብረ-ንቦች መለያ ይሰጣል፡፡

4) አግባብ ያለው አካል አናቢው ሀብረ-ንቡን እንዳስመዘገበ መለያ መስጠት አለበት፡፡

5) ማንኛውም አናቢ አግባብ ካለው አካል መለያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ ቀፎው ላይ ማድረግ አለበት፡፡

6) አናቢው እስመዝግቦት የነበረ ሀብረ-ንብ በተለያዩ ምክንያቶች ቀፎውን ለቆ የሄደ ከሆነ ከለቀቀበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው አካል ማሳወቅ ያለበት ሲሆን አግባብ ያለው አካልም መለያውን ይሰርዛል፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ሀብረ-ንብ ቀፎው ውስጥ የገባበት ወይም ያስገባ አናቢ የሀብረ-ንቡ ባለቤት ስለሚሆን በእጁ በገባ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው አካል ማስመዝገብ አለበት፡፡

2) The beekeeper who registers the bee colony under sub-article 1 of this article shall register any new additional colony obtained by purchase, gift, and multiplication or swarming by the appropriate body within fifteen days from the date he places the new bee colony in the beehive.

3) The appropriate body shall give identification to honeybee colonies for national information.

4) The appropriate body shall give identification upon registration of bee colonies

5) Any beekeeper shall place identification obtained from the appropriate body on the beehive, within three days from the date of issuance of the identification.

6) A Beekeeper whose bee colony has left the hive for various reasons shall notify the appropriate body within fifteen days from the date the bee colony has left the hive, and the appropriate body shall cancel the identification.

7) Without prejudice to the provisions of sub- Article 6 of this Article, a beekeeper whose colony enters his hive or transfers the colony by himself, shall be the owner and register the colony by

**4. የማነቢያ ስፍራ አወሳሰን**

1) በከተማ ንብ የማነብ ስፍራ ሲወሰን አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. ለንብ ቀሰምንት ጠቃሚ የሆኑና በተለያዩ ወቅቶች የሚያብቡ ዕፅዋቶች በአካባቢው መኖር ወይም ማልማት፤

ለ. ንፁህ ውሃ በማነቢያ ስፍራ ውስጥ ማቅረብ መቻሉን ማረጋገጥ፤

ሐ. መሬቱ ረግረጋማ ያልሆነና በጎርፍ የማይጠቃ መሆኑን፤

መ. ለትራንስፖርት አመቺ መሆኑን፤

ሠ. ከማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር ከሚያልፍበት፣ ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት ቦታ እና ከመኖሪያ አካባቢ ቢያንስ 50 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፤

the appropriate body within fifteen days of the entry.

**4. Apiary Site Determination**

1) The appropriate body shall ensure that the following requirements are met when determining an urban apiary site:

a) Presence of important honey bee flora and Plants that bloom in different seasons in the area or be able to develop honey bee flora.

b) Ensure that clean water can be provided in the apiary site.

c) The land is not swampy and flood-affected.

d) Accessible to transport.

e) At least 50 meters away from social service-providing institutions, residential areas, high-electricity lines, garbage, and sewerage areas.

ረ. የማናቢያ ስፍራው የመብረሪያ አቅጣጫ ከ3 ሜትር ያላነሰ ከፍታ ባለው የግንብ፣ የንብ ቀሰም እፅዋት ወይም የጠቅጣቃ ሽቦ አጥር በማጠር ህብረ-ንብ ያለበትን ቀፎ መቀመጡን፤

ሰ. ኬሚካል ከሚያበኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2 ኪ.ሜ የራቀ መሆኑን፤

ሸ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በብዛት የማይካሄድበት አካባቢ መሆኑን፤

f) The beehive shall be placed in the apiary site fenced with a wall, bee flora plant or wire meshes no less than 3 meters from the flight direction.

g) At least 2 km away from factories that releases chemicals.

h) It should be an area of no frequent chemical application.

2) በገጠር ንብ የማነብ ስፍራ ሲወሰን አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት

2) The appropriate body shall ensure that the following requirements are

መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. ለንብ ቀሰምንት ጠቃሚ የሆኑና በተለያዩ ወቅቶች የሚያብቡ ዕፅዋቶች በአካባቢው መኖር ወይም ማልማት፤

ለ. ንፁህ ውሃ ከ0.5 እስከ 1 ኪ.ሜ መኖሩን ወይም በማነቢያ ስፍራ ውስጥ ዉሃ ማቅረብ መቻሉን ማረጋገጥ፤

ሐ. መሬቱ ረግረጋማ ያልሆነና በጎርፍ የማይጠቃ መሆኑን፤

መ. ለትራንስፖርት አመቺ መሆኑን፤

ሠ. ከማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር ከሚያልፍበት፣ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት ቦታ 100 ሜትር የራቀ መሆኑን፤

ረ. የማነቢያ ስፍራው ከመኖሪያ ቤት 50 ሜትር መሆኑን፤

ሰ. ኬሚካል ከሚያቦኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2 ኪ.ሜ የራቀ መሆኑን፤

ሸ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በብዛት የማይካሄድበት አካባቢ መሆኑን፤

3) የንግድ ንብ ልማት የማነብ ስፍራ ሲወሰን አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. ከማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር ከሚያልፍበት፣ ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት እና ከመኖሪያ ቤት 100 ሜትር የራቀ መሆኑን፤

met when determining a rural apiary site:

a) Presence of important honey bee flora and Plants that bloom in different seasons in the area or the beekeeper can develop honey bee flora.

b) Availability of clean water at a distance of 0.5 to one km from the apiary site or able to provide clean water in the apiary site.

c) The land is not swampy and flood-affected.

d) Accessible to transport.

e) At least 100 meters away from social service-providing institutions, high-electricity lines, garbage, and sewerage areas.

f) At least 50 meters away from residential areas.

g) At least 2 km away from factories that release chemical.

h) Place where repeated pesticide spray should not be widely used.

3) The appropriate body shall ensure that the following requirements are met When determining commercial beekeeping development apiary site:-

a) At least 100 meters away from social service-providing institutions, residential areas, high-electricity lines, garbage, and sewerage area.

ለ. ኬሚካል ከሚያቦኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2 ኪ.ሜ የራቀ መሆኑን፤

ሐ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በብዛት የማይካሄድበት አካባቢ መሆኑን፤

መ. ከሌላ የንግድ ንብ ልማት ጣቢያ ቢያንስ ከ 3 ኪ.ሜ ርቀት ያለው መሆኑን፤

ሠ. ለማናቢያ የሚገለግሉ የተሟሉ ቁሳቁሶች መኖራቸውን፤

ረ. እራሱ የሰለጠነ እና የምስክር ወረቀት ያለው ወይም የሰለጠነና የምስክር ወረቀት ያለው ሰው ቀጥሮ ማሰራት አለበት፤

ሰ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከ ሀ እስከ መ የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት::

b) At least 2 km away from factories which release chemicals;

c) Place where repeated pesticide spray should not be widely used

d) At least 3 km away from another commercial bee-keeping development center.

e) Availabilities of necessary beekeepi equipment.

f) The owner shall be trained and has a certificate; or hire a trained person who has a certificate.

g) Meet requirements listed in sub-article 2 (A-D) of this article.

**5.የህብረ-ንቦች ውደት**

1) ማንኛውም በውደት ላይ የተገኘ ህብረ-ንብ ከአረፈበት ቦታ በሚያዝበት እና ወደ ተዘጋጀለት ቀፎ ለማስገባት ሲጓጓዝ አስፈላጊውን ሙሉ የንብ መከላከያ አልባሳትና የውሃ ርጭት በመጠቀም በጠቅጣቃ ሽቦ ወይም አየር ሊያስገባ በሚችል ጨርቅ በመሸፈን ንቦችን በማይጎዳ መልኩ መሆን አለበት፤

2) ወደ ቀፎ ማስገባት ካልተቻለ ንቦቹን በማያስወጣና አየር ሊያስገባ በሚችል ጠቅጣቃ ሽቦ፣ ጨርቅ፣ ሰሌን፣ ካርቶን መጓጓዝ አለበት::

**5. Honeybee Colony Swarm**

1) When catching a swarming colony from the landing place and transporting it to the desired area, it shall be carried out in a manner that does not harm bees by using the necessary protective clothing and water spray by covering it with light mesh wire sheet or woven fabric seal that allow adequate air into the container.

2) If it is not possible to put it in the hive, the bees shall be transported in a well-ventilated compact wire, cloth, cellophane, and cardboard.

## ክፍል ሶስት

## የንግስት ንብ ርቢ፣ የማነቢያ መሣሪያዎች ማምረትና ምርምር

### 6. የንግድ ንግስት ንብ ርቢ

1) ማንኛውም የንግድ ንግስት ንብ ርቢ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

2) ማንኛውም በንግስት ንብ ርቢ ንግድ ስራ የተሰማራ ሰው ከተቆጣጣሪ አካል ንግስት ንብ የማባዛትና የማሰራጨት ወይም የማባዛትና የመሸጥ ፍቃድ ተሰጥቶአቸው ከሚሰሩ ማዕከላት ለመነሻ እናት ንብ መጠቀም አለበት፡፡

3) ለንግድ ለንግስት ንብ ርቢ የሚውል ጣቢያ ወይም ማዕከል ለማቋቋም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን የመምረጫ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ. በመካከላቸው ቢያንስ 300 ሜትር ርቀት ያላቸው ሁለት የቀፎ ማስቀመጫ ጥላ/ጋጣ/ ማዘጋጀት፤

ለ. ለንግሥት ንብ ማራቢያ የሚያገለግሉ የተሟሉ ቁሳቁሶች መኖር፤ እና

ሐ. በንግስት ንብ አርቢ እራሱ የሰለጠነ እና የምስክር ወረቀት ያለው ወይም የሰለጠነና የምስክር ወረቀት ያለው ሰው ቀጥሮ

## Part Three

## Queen Bee Rearing, Beekeeping Equipment Production and Research

### 6. Commercial Queen Bee Rearing

1) Any person interested in running commercial queen bee rearing shall fulfil the requirements stipulated for a certificate of competency.

2) Any person who is engaged in commercial queen bee rearing shall use the initial Parental Stock of Queen bee from centers that are licensed by a regulatory body to reproduce, distribute, and sell Queen Bees.

3) In addition to fulfilment of the provisions of sub-Article 3 of Article 4 anyone who wants to establish a commercial queen bee rearing center or station, shall fulfil the following selection criteria:

a) Prepare at least two apiary shades which are placed at a distance of at least 300 meters apart.

b) Prepared complete equipment required for queen bee rearing, and

c) The owner shall be trained and certified or hire trained and certified person.

ማስራት አለበት።

## 7. የማነቢያ መሳሪያዎች ማምረት

1) ለቅድመ-ምርት አገልግሎት የሚውሉ ማናቸውም የንብ ማነቢያ መሳሪያዎች ማምረት ላይ የተሰማራ ሰው ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ማምረት አለበት።

2) ለድህረ-ምርት አገልግሎት የሚውሉ ማናቸውም የማቀነባበሪያና ማከማቻ መሳሪያዎች ማምረት ላይ የተሰማራ ሰው ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ማምረት አለበት።

3) በአገር ውስጥ የሚመረቱትና ከውጪ የሚገቡ የንብ ማነቢያ፣ የማቀነባበሪያና ማከማቻ መሳሪያዎች ጥራትና ደረጃቸውን ጠብቀው ለገበያ መቅረባቸውን በተቆጣጣሪው አካል ቁጥጥር ይደረግበታል።

## 7. Beekeeping Equipment production

1) Any person engaged in the manufacturing of pre-harvest equipment shall produce and supply for the market in accordance with the criteria set by the regulatory body.

2) Any person engaged in the manufacturing of post-harvest processing and storage equipment shall produce and supply for the market in accordance with the criteria set by the regulatory body.

3) Locally produced and imported processing and storage equipment shall be inspected by the regulatory body for their quality and standards.

## 8.የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

ማንኛውም ሰው በንግድ ንብ ልማት፣ ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ተቆጣጣሪውን አካል ሳያስፈቅድ የድርጅቱን ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር ወይም የባለቤትነት ለውጥ ማድረግ አይችልም።

## 8. Change of Address and Ownership

Any person engaged in commercial beekeeping development, queen bee rearing station or center; beekeeping equipment and materials production, honey bee product processing and packaging plant should not change the address and ownership where he received the certificate of competency assurance without the permission of the regulatory body.

## 9.በንብ ዝርያ ማሻሻል፣ የማናቢያ መሳሪያዎች እና በንብ ውጤቶች ላይ ምርምር ስለማካሄድ

## 9. Research on Honeybee Species Improvement,Beekeeping Equipment and Honeybee Products

1) ማንኛውም የውጪ አገር ዜጋ በንብ ዘር ማሻሻል፣ በንብ ውጤቶች፣ በማር ዕፅዋትና በንቦች አጠቃላይ እንክብካቤ ላይ ምርምር ለማካሄድ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. ማንነቱን የሚገልፅ መረጃ፣ የመጣበትን ዓላማ እና የቆይታ ጊዜውን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ አለበት፤

ለ. በንብ ሀብት ልማት ስፔሻላይዝድ ያደረገበት ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፤

ሐ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1(ለ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተመራማሪው በትምህርት ሂደት ላይ እያለ ከሆነ የተማሪነት ማስረጃ ማምጣት አለበት፤

መ. ምርምር ለማካሄድ በሚመጣበት ወቅት ከሀገር ውጪ ያሉ የንብ ዝርያዎችን ይዞ አለመምጣቱን ስልጣን በተሰጠው አካል መረጋገጥ አለበት፤

ሠ. ለምርምሩ የሚረዱ የምርምር ቁሳቁሶች ካሉት ስለትክክለኛነታቸው ስልጣን በተሰጠው አካል ማስፈተሽና ማስመዝገብ እንዲሁም እቃውን ለማስገባት የተሰጠውን ፍቃድ ማያያዝና ማቅረብ አለበት፤

ረ. በንብ ዘር ማሻሻል የምርምር ስራ ሊያካሂድ የሚችለው የንብ ንዑስ ዝርያዎች በሚገኙበት ስነ-ምህዳር ክልል ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፤

ሰ. ስለሚመራመረው ነገር ዝርዝር ሁኔታ የሚገልፅ ዝርዝርየስራ ዕቅድ ማቅረብ አለበት፤

1) Any foreigner seeking a license from the regulatory body to conduct research on honeybee species improvement, honeybee products, honeybee flora, and general honeybee management shall meet the following requirements:

a) Provide the concerned body with personal identification, purpose of arrival, and duration of stay.

b) Provide evidence of specialization in honeybee resource development.

c) Notwithstanding the provisions of sub-article 1 (b) this this Article, the researcher must provide proof of student status while learning;

d) Up on arrival for research works, it should be verified by an authorized body that no honeybee species are brought in from abroad by the same.

e) Any research materials brought from abroad shall be inspected and registered by an authorized body and a permit to import the research materials shall be attached and submitted.

f) Research on honeybee species improvement shall only be conducted in the ecological niche where the honey bee sub-species are located;

g) He shall provide a work plan outlining the details of his research.

| | |
|---|---|
| ሸ. በቆይታ ጊዜ ውስጥ የሀገሪቱን የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ህጎችና ሌሎች ህጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፤ | h) He shall be obliged to comply with the country's Apiculture Resource Development and Protection and other laws during his stay. |
| ቀ. ምርምር ለማድረግ በሚሄድባቸው ቦታዎች በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ማንነቱን የሚገልፅ መረጃ መያዝና በሚሄድበት ወቅት ለሚመለከተው አካል የሚዘዋወርባቸውን አካባቢዎች የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤ | i) Obliged to carry his identification while traveling for research works, and to notify and disclose the place of his travel to concerned bodies. |
| በ. የምርምር ስራውን እንዳጠናቀቀ ውጤቱን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፤ | j) Obliged to present the results to concerned bodies upon completion of the research work. |
| 2) ከምርምር ውጤት በኋላ የሀገሪቱን የንብ ዝርያዎች ይዞ መውጣት የተከለከለ ነው፡፡ | 2) It is prohibited to take away the country's honeybee species after completing the research. |
| **<u>10. የንብ ዘርን በማዳቀል ስለማሻሻል</u>** | **<u>10. Honeybee Species Improvement through Crossbreeding</u>** |
| 1) ማንኛውም የንብ ዘር በማዳቀል የዝርያ ማሻሻል ስራ ሊከናወን የሚችለው በመንግስት ስልጣን በተሰጠው ተቋም ወይም አካል ፍቃድ በተሰጣቸው የግልና የማህበር ተቋም በተቆጣጣሪው ብቻ ይሆናል፡፡ | 1) Any honeybee species improvement through crossbreeding shall be done by an institution authorized by the government or by a private and association institution licensed by a regulatory body. |
| 2) ማንኛውም የንብ ዘር በማዳቀል የዝርያ ማሻሻል ስራ የሚሰራ ሰው የሀገሪቱን የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ እና ሌሎች ህጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ | 2) Any person engaged in honeybee species improvement through crossbreeding shall be obliged to comply with the Apiculture Resource Development and Protection law and other laws of the country. |
| 3) በማዳቀል የሚገኝ የተሻሻለ አዲስ የንብ ዘር የሚመዘገበው በብሔራዊ ደረጃ | 3) Newly improved crossbred honeybee species shall be registered by |

በሚቋቋመው በዝርያ ወይም ዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ግምገማ ውጤት መሠረት በተቆጣጣሪ አካል ሲፀድቅ ነው፡፡

4) በማዳቀል የሚገኝ የተሻሻለ አዲስ የንብ ዘርን ያገኘ ማንኛውም ሰው የተሟላ የርቢ መረጃን ለዝርያ ወይም ለዘር አጽዳቂ ኮሚቴ በመስጠት የማጸደቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 11. በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር ስለ መመዝገብ

1) ማንኛውም በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር መመዝገብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 መሰረት በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር መመዝገብ የሚችለው፡-

ሀ) በዋናኛነት ምርታማነታቸው፣ እነስተኛ የመናደፍ ባህሪያቸው፣ የቀፎ ውስጥ ፅዳት ችሎታቸው፣ እነስተኛ ዑደትና ኩብለላ፣ በሽታንና ድርቅን የመቋቋም አቅማቸው እና አካባቢውን የመላመድ ብቃታቸው በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ለ) አዳቃዩ ይመዝገብልኝ ብሎ ከጠየቀበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላቸው የምርታማነትና ሌሎች ባህሪያቶች ታይተው ለንብ ሀብት ልማት ይውላሉ ተብሎ ከታመነባቸው ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተዳቀሉ ንብረ-ንቦችን በተመረጡ አናቢዎችና በማስልጠኛ

an authorized regulatory body on the evaluation results of a nationally established breed approval committee.

4) Any individual that has acquired newly improved honeybee species through crossbreeding is obliged to provide full records of the new breed and get it approved by an approval committee

## 11. Registration of Honeybee Obtained through Crossbreeding

1) Any honeybee species obtained by crossbreeding shall be registered.

2) Subject to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, any honeybee species obtained by crossbreeding shall be registered when:-

a) Its productivity, less aggressive behaviour, ability to clean the hive, less tendency of swarming and absconding, disease and pest resistance, and the ability to adapt to the environment is verified by a concerned regulatory body.

b) Productivity and other behaviours are evaluated to be useful for apiculture resource development after being tested for two years from the date the breeder requests for registration.

3) Subject to the provisions of Sub-Article 2(b) of this Article, crossbred honeybees may be distributed when their productivity is tested by selected

ተቋማት ላይ ሙከራ በማድረግ ውጤታማነታቸው በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ከተረጋገጠ በኋላ ማሰራጨት ይቻላል፡፡

beekeepers and training institutes that the regulatory body selects.

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዳቀል የተገኙት ንቦች ውጤታማ ካልሆኑ ምዝገባው አይካሄድም፡፡

4) Subject to the provisions of sub-article 3 of this Article, if honeybees obtained by crossbreeding are found ineffective shall not be registered.The honeybees shall be removed before further damage.

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተዳቀሉት ንቦች ሌላ ጉዳት እንደሚያደርሱ በተቆጣጣሪው አካል ከተረጋገጠ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

5) Subject to the provisions of sub-article 4 of this Article, the new crossbreed honeybees shall be culled if the regulatory body assures their harmfulness.

## ክፍል አራት

## የንብ ውጤቶች አቀነባበር፣ አስተሻሸግ፣ አያያዝ፣ ምልክት አደራረግና አጓጓዝ

## Part Four

## Honey bee Products Processing, Packaging, Handling, Labelling and Transporting

### 12.ስለንብ ውጤቶች ማቀነባበርያና ማሸጊያ የህንፃ ግንባታ

### 12. Construction ofHoneybee Products Processing and Packaging Building

ለንብ ውጤቶች ማቀነባበርና ማሸግ አገልግሎት የሚውል ህንፃ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

A building used for the processing and packaging of honeybee products shall meet the following requirements:

1) የሚገነባው ህንፃ ቢያንስ የሰራተኞች ንፅህና መጠበቂያና ልብስ መቀየሪያ ክፍል፣ ያልተጣራ የንብ ውጤቶች ማከማቻ ክፍል፣ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ ማሸጊያና ሌብል ማድረጊያ ክፍል፣ የተጣራ የንብ ውጤቶች ማከማቻ ክፍል፣ አነስተኛ ላብራቶሪ፣ የዕቃዎች ማከማቻ ክፍል፣ ጽ/ቤት እና የፍሳሽ ማስወገጃ ማሟላት አለበት፤

1) The building to be constructed shall at least have an employees' Hygiene protection and Clothing changing room, crude Honeybee product Storage room, Honeybee product Processing, Packaging, and Labelling room, processed Honeybee product storage room, medium laboratory, office, and sewerage disposal.

| | |
|---|---|
| 2) የሚገነቡት ክፍሎች በቀላሉ ማፅዳት እንዲቻል ወለሉና ግድግዳው መታጠብ የሚችል እንዲሁም ሙቀትና ዕርጥበት ለመቆጣጠር አየር እንዲያዘዋውርና መርዛማ ካልሆኑ ቁሳቁሶች መገንባት አለበት፤ | 2) The building room floors and walls should be washable, able to control temperature and humidity, circulate air, and constructed from non-toxic materials. |
| 3) የንብ ውጤቶች ሲከማቹ ከወለሉ ጋር ቀጥታ ግንኙነት እንዳይኖረው ወለሉ ላይ መደርደሪያ ሊኖር ይገባዋል፤ | 3) When honeybee product is stored, there should be a shelf to avoid direct contact with the floor; |
| 4) ለንብ ውጤቶች ማቀነባበር የሚውል ህንፃ የሚገነባበት ቦታ የንብ ውጤቶችን ከሚበክሉ ባዕድ ነገሮች 50 ሜትር መራቅ አለበት፤ | 4) The building site for honeybee products must be 50 meters away from foreign pollutants. |
| 5) ለንብ ውጤቶች ማቀነባበር የሚውል ህንፃ የሚገነባበት ቦታ ከፋብሪካ ጭስ ቢያንስ 2 ኪ.ሜትር የራቀ መሆን አለበት፤ | 5) The building should be at least 2 km awayfrom foreign materials and factory smokewhichpollutes honeybee products; |
| 6) ለንብ ውጤቶች ማቀነባበር የሚውል ህንፃ በሚገነባበት ቦታ መሰረታዊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች የተሟሉበት ወይም ባለቤቱ ማሟላት የሚችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤ | 6) It shall be ensured that the basic infrastructure is available in the area where honeybee product processing is built or the owner fulfils the necessary infrastructure |
| <u>13. ስለንብ ውጤቶች ማቀነባበርያ፣ ማሸጊያ ቁሳቁሶችና ስለምልክት አደራረግ</u> | **<u>13. Honeybee Products Processing, Packaging Equipment and Labelling</u>** |
| 1) ማንኛቸውም ለንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ የሚውሉ ቁሳቁሶች ተቆጣጣሪው አካልና ደረጃ ለማውጣ ስልጣን የተሰጠው አካል ባወጣው ደረጃ መሰረት መስፈርቱን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡ | 1) Any Materials used for processing and packaging of bee products shall meet criteria set by the regulatory body. |
| 2) ማንኛውንም የንብ ውጤት በማቀነባበርና ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ከተመሳሳይ አካባቢዎች በተመሳሳይ ወቅት የሚሰበስባቸው የንብ ውጤቶች ለይቶ ማቀነባበርና ማሸግ | 2) Any person engaged in processing and packaging shall identify and process the bee products collected from the same area at the same time; |

አለበት፡፡

3) ማንኛውንም የንብ ውጤት አቀነባብሮና አሽጎ ለገበያ የሚያቀርብ ሰው በማሸጊያ እቃው ላይ ተቆጣጣሪው አካል ባወጣው መስፈርት መሰረት ስለምርቱ የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ መለጠፍ አለበት፡፡

3) Any person engaged in honey bee product processing, packaging and supply to the market shall label full information about the product in accordance with the requirements set by the regulatory body.

**14. ስለ ንብ ውጤቶች ምርት አከመቻቸትና አጓጓዝ**

**14. Honeybee Products Storage and Transportation**

1) ማንኛውም የንብ ውጤቶች የሚከማችበት ቦታ ንፅህናው በተጠበቀና ደረቅ ፣ለፀሐይ ብርሃን ያልተጋለጠና በቂ የአየር ዝውውር ባለው ቦታ መሆን አለበት፡፡

1) Any place where honeybee product is stored shall be clean, dry, and not exposed to sunlight and with adequate ventilation;

2) ማንኛውም የንብ ውጤቶች መያዣና ማከማቻ ዕቃ ንፅህናው በጠበቀ ደረቅ፣ ምንም ዓይነት ሽታ የሌለው፣ አየር በማያስገባ መልኩ የሚከደንና ለዚህ ስራ የተፈቀዱ ቁሳቁሶች መሆን አለባቸው፡፡

2) Any store and container of honeybee products shall be clean, dry, odourless, airtight, and approved for this purpose;

3) ማንኛውም ሰው የንብ ውጤቶች በሚያጓጉዝበት ወቅት የሚከተሉትን የንፅህና መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

3) Any person who transports bee products shall fulfil the following hygiene requirements:

ሀ) ማጓጓዣውን የንብ ውጤቶች ከመጫኑ በፊት ማጽዳትና ከሌሎች ማጓጓዣ መለየት፤

ለ) የመጫኛ መሳሪያ ማጽዳትና ንፁህ ማድረግ፤

ሐ) በበሽታ ወይም በሕመም ማለትም በተቅማጥ፣ በአጣዳፊ የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽን፣ በሳልሞኔላ፣ ሺጌላ ዝርያ፣ ኢ.ኮሊ ዝርያ፣ ሄፒታይተስ ኤ ቫይረስ ምክንያት በተከሰተ በሽታ እና በምግብ ሊተላለፉ የሚችሉ ሌሎች ኢንፌክሽኖች የተያዘ ማንኛውም ሰው የንብ ውጤቶች በሚጫኑበት ወቅት ወደ ማጓጓዣው እንዳያጓጉዝ ወይም እንዳይጭን ማድረግ፤

መ) ዕርጥበት ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ የንብ ውጤቶች መያዣ

a) Clean and separate the conveyance from other conveyances before loading bee products.

b)Clean and sanitize loading equipment

c) During loading any person suffering from disease or illness such as diaherria,acute respiratory infection,disease caused by salmonella, shigellaspecies, E.coli species, hepatitis A Virus, and other infections that can be transmitted through food shall not transport or load bee products to the conveyance.

d) Use bee product containers prepared in such a way as to prevent moisture.

ዕቃዎች መጠቀም፣በተገቢው ቦታ መቀመጥ አለባቸው፤

ሠ) ውሃ የማይቆጥሩ ሸራዎች ወይም ሌሎች ተስማሚ ሽፋኖች መጠቀም፤

4) ማንኛውም የንብ ውጤቶች በሚጓጓዝበት ወቅት ከሌሎች የንብ ውጤት ካልሆኑ ምርቶች ጋር መጫን አይፈቀድም፡፡

## ክፍል አምስት

**የንብ ሀብትና የንብ ቀሰም ዕጽዋት አጠባበቅ እና የአናቢ ግዴታ**

### 15. የንብ ሀብት ጥበቃ

1) ማንኛውም የዕፅዋት ጥበቃና ሌሎች ስራዎችን የሚያካሂድ ሰው ፀረ-ተባይ እና ሌሎች ኬሚካሎችን መጠቀም ያለበት ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ብቻ መሆን ያለበት ሲሆን መጠቀም ግዴታ ሆኖ ከተገኘ በሚጠቀምበት ወቅት አግባብ ባልሆነ አጠቃቀም ምክንያት ንቦችንና የንብ ጤጤቶች እንዳይመረዙና በንቦች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚከተሉትን ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

ሀ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭትን በሰው ጉልበት፣ በመኪና ወይም በአይሮፕላን በሚያከናውንበት ወቅት ቢያንስ በ4 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ንቦች መኖራቸው ከተረጋገጠ ከ72 ሰዓት በፊት ለንብ አናቢዎች ወይም ለሚመለከተው አካል መቼ፣ የት ቦታ እና

e) Shall Use Waterproof tarpaulins or other suitable coverings.

4) It is not allowed to transport honeybee products together with other non-bee products.

## Part Five

**Apiculture Resource and Honeybee Flora Protection and Obligation of Beekeeper**

### 15. Protection of Apiculture Resource

1) Any person who carries out plant protection and other activities shall use Pesticides or other chemicals only if there is no other alternative and if the pesticide is necessary to use, the following precautions should be taken to reduce poisoning to bees and bee products and damage to bees:

a) Spraying of pesticides used by human labor, cars, or airplanes shall inform beekeepers and concerned body when, where, and at what time, for how much time, and what kind of chemical will be sprayed at least before 72 hours when it is confirmed that there are honeybees in

| | |
|---|---|
| በስንት ሰዓት፣ ለምን ያክል ጊዜ እና ምን አይነት ኬሚካል እንደሚረጭ ማሳወቅ አለበት፤ | the area around 4 km; |
| ለ. የኬሚካል ርጭቱ በንብ እርባታው አቅራቢያ ባሉ የሰብል ማሳዎች ላይ አረሞች ሣያብቡ ወይም ከቀኑ 11 ሰዓት በኋላ መካሄድ አለበት፤ | b) Spraying shall be done in cultivation lands and weeds growing alongside the border near the apiary site before flowering or after 5 pm. |
| ሐ. በሰብል ላይ የሚረጩ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የቆይታ ጊዜያቸው አጭር ሆኖ ተባዮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ መቆጣጠር የሚችሉና ከአካባቢ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው፤ | c) Use chemicals that are less harmful to bees, stay for a short period on the plant, effective and environmentally friendly. |
| መ. በጥቅም ላይ የሚውሉት ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በተቆጣጣሪው አካል የተመዘገቡና የአጠቃቀም መመሪያ በመያዣ እቃዎቻቸው ላይ ያላቸው መሆን አለባቸው፤ | d) Use pesticide chemicals that are registered by the regulatory body and have instructions manual on their container. |
| ሠ. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከመጠቀሙ በፊት የአጠቃቀም መመሪያውን በደንብ ማወቅ እና መጠቀም አለበት፤ | e) Know the instruction manual before using pesticides. |
| ረ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በሚካሄድበት ወቅት ከፍተኛ ነፋስ የሚኖር ከሆነ ኬሚካሉ በንቦች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ምንም ዓይነት ርጭት መካሄድ የለበትም፤ | f) If there is a high wind during the spraying of pesticides; no spraying should be done to prevent the chemicals from damaging the bees. |
| ሰ. ለኬሚካል ርጭት ጥቅም ላይ የዋሉ መርጫ መሳሪያዎች፣ አልባሳት እና የተለያዩ ቁሳቁሶች ታጥበው እና ደርቀው በተገቢው ቦታ መቀመጥ አለባቸው፤ | g) Materials used for spraying chemicals, clothing & different materials shall be washed, dried, and put in an appropriate place; |
| ሸ. የቁሳቁሶች አጣቢ ንቦች ባሉበት አቅራቢያና በውሀ አካላት ላይ እንዳይደፉ በማድረግ በጥንቃቄ መወገድ አለበት፤ | h) Material wastes should be carefully removed to prevent contact with bees and water bodies: |
| ቀ. ባዶ የፀረ ተባይ መያዣ ዕቃዎችን ሶስት | i) Empty pesticides should be rinsed three |

| | |
|---|---|
| ጊዜ በውሃ በማለቅለቅ ተበሳስተው እንዲቀመጡና ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መወገድ ይኖርባቸዋል፤ | times with water and disposed of in accordance with the authority directive. |
| ቡ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭቱን የጊዜ ሠሌዳ እንደ አካባቢው የአየር ንብረት ተለዋዋጭነት በመከታተል እንዲቀያየር ማድረግ አለበት። | j) Shall adjust the spray schedule according to local climate conditions. |
| 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ለመተግበር በሰብል፣ በእንስሳት፣ በአካባቢ ጥበቃ እና በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ተሰማርተው የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መስራት አለባቸው:: | 2) Stakeholders who work on crop, animal, and environmental and natural resources shall work together to implement tasks enumerated under sub-article 1 of this article; |
| 3) የተቀነባበሩ የንብ መኖዎች በሀገር ውስጥ ለማምረት ወይም ከውጭ ሀገር ለማስገባት የሚፈልግ ሰው ከሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል:: | 3) A person who wants to produce or import Processed bee feed shall acquire a certificate of competency from the regulatory body. |
| 4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጪ የሚገቡና በሃገር ውስጥ የሚመረቱ የተቀነባበሩ የንብ መኖዎች ተቆጣጣሪው አካል የሚያወጣውን መስፈርት ማሟላት አለበት:: | 4) Subject to the provisions of Sub-Article 3 of this Article, imported processed honeybee feed shall meet the requirements that are set by the concerned regulatory body. |
| <u>16. የንብ ቀሰም ዕፅዋት ጥበቃ</u> | **<u>16. Protection of Honeybee Flora</u>** |
| 1) ማንኛውም ሰው ለምርምር ወይም ለሌላ ተግባር የማር ዕፅዋት ዝርያዎችን ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ሲፈልግ ከተቆጣጣሪው አካል የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት:: | 1) Any person who wants to import honeybee flora species for research or other purpose shall obtain a certificate of competency from the regulatory body. |
| 2) የማር ዕፅዋት ዝርያው ለተጠቃሚዎች ከመሰራጨቱ በፊት በተለያዩ ስነ ምህዳሮች ሙከራ ከተደረገ በኋላ ውጤታማነቱ በተቆጣጣሪ አካል መረጋገጥ አለበት:: | 2) The effectiveness of honeybee flora shall be tried in different agro-ecology by the regulatory body before it is distributed to beekeepers. |

## 17. የእናቢ ግዴታዎች

1) ማንኛውም እናቢ የንብ እርባታ ሲያካሂድ በንቦች ላይ ጉዳትና እልቂት እንዳይደርስ የሚከተሉት ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡፡

ሀ. እናቢው የተሟላ የንብ መከላከያ ትጥቅ ማለትም ቱታ፣ ቦት ጫማ፣ ጓንት እና አይነርግብ እና ሌሎች መከላከያዎችን መጠቀም፤

ለ. ንቦችን የሚያስቆጣ ሽቶ፣ ከፍተኛ ጭስ፣ ፊካ ያላሉና ንፅህናቸው ያልተጠበቁ አልባሳት፣ ማሩን የሚበክል የኩበት ጭስ፣ ኬሚካል እና ሌሎች ነገሮችን አለመጠቀም፤

ሐ. እናቢው የግልና የጋጣውን ስፍራ ንፅህና መጠበቅ ፤

2) ማንኛውም እናቢ የኬሚካል ርጭት በአካባቢው እንደሚደረግ በተገለፀለት ጊዜ ምን አይነት ኬሚካል እንደሚረጭ ከባለሞያ ካረጋገጠ በኋላ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡፡

ሀ. የኬሚካሉ ባህሪ ከተረጨ በኋላ ቅሪቱ ለረጅም ሰዓታት (ከ 24 ሰዓት በላይ) በተክሉ እና አካባቢው ላይ የሚቆይ መሆኑ ከታወቀ ህብረ-ንቡን ከሚረጭበት ቦታ ቢያንስ 5 ኪሎሜትር ርቀት ቦታ በመውሰድ እንደ ሁኔታው ለ1 ሳምንት ማቆየት አለበት፤

ለ. ኬሚካሉ ከተረጨ በኋላ ቅሪቱ ከ24 ሰዓት በታች ጊዜ የሚቆይ መሆኑ ከታወቀ ህብረ-

**17. Obligations of Beekeeper**

1) Any beekeeper shall take the following precautions to prevent damage and death of honeybees during beekeeping practice:

a) The beekeeper shall be fully equipped with protective clothes such as overalls, boots, gloves, veil, and other protective.

b) Not using perfume, smoke, dark and unclean clothes that irritate honeybees and dung smoke, chemicals and other things that contaminate honey.

c) The beekeeper shall keep his personal and hive shade hygiene.

2) When the beekeeper is informed that chemical spraying will be carried out, he shall take the following precautions after confirming the type of chemical to be sprayed from experts:

a) If it is known that the nature of the chemical remains on the plant and its surroundings for long hours (more than 24 hours) after it is sprayed, the honeybee's colony shall be placed at a distance of at least 5 kilometres from the spraying location for 1 week;

b) The beekeeper shall keep the colony inside the hive and feed it for a day if the duration of spraying chemical residue is

ንቡን ለ1 ቀን ከቀፎው እንዳይወጡ አድርጎ በመመገብ ማቆየት አለበት፤

known to be staying for less than 24 hours.

3) የማነብ ስራ የሚያካሄድ ማንኛውም አናቢ ሕብረ-ንቦቹ በሰው እና በቤት እንስሳት ላይ አደጋ እንዳያደርሱ የሚከተሉትን ቅድመ ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡-

3) Any beekeeper shall take the following precautions to prevent the negative impacts of honeybees on humans and domestic animals:

ሀ. በአካባቢው የንቦች ቁጣን ሊያስከትል የሚችል ሽታ ማለትም ሽቶ፤ ትኩስና የከረመ የእዛበ ሽታ፤ አዲስ የተቆፈረ የመሬት ሽታ እና ሌሎች ሽታዎች እና ከፍተኛ ድምፅ እንዳይኖር ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

a) Care should be taken that the area is free from odors that can irritate bees such as perfume, dung, newly dug soil odor, and other odors and sound disturbances.

ለ. በአካባቢው ንብ የማነብ ስራ ስለመኖሩ የሚገልፅ በቢጫ መደብ ላይ በጥቁር ቀለም የሰራተኛ ንብ ምስል ያለበት በግልፅ የሚታይ ልዩ ምልክት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

b) There should be a visible picture of a worker bee in black on a yellow background indicating the presence of beekeeping activity in the area

4) ሁብረ-ንቦችን በማዟዟር የሚያናባ አናቢ ንቦችን ማዟዟር የሚችለው የንብ ንዑስ ዝርያዎች በሚገኙበት ስነ-ምህዳር ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡

4) any beekeeper should undertake migratory beekeeping in the ecological niche where the honeybee sub-species are located.

5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አናቢ ሁብረ-ንቦቹን ከማዟዟሩ በፊት ሁብረ-ንቡ ከበሽታ ማለትም አሜባ፤ ኖሴማ እና ከተባዮች ማለትም የሰምበል ትል፤ የንብ መዥገር እና ከንብ ቅማል በተለይ ከቫሮዋ ቅማል ነጻ መሆናቸው በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡

5) Notwithstanding the provisions of sub-Article 4 of this Article, any beekeeper who wants to transport a honeybee colony from place to place should get first permission from an expert that assures the colony is free from diseases such as amoeba, nosema, pests such as wax moth, bee ticks, and bee mite, especially varroa mite.

6) በውደት ወቅት ከሌላ ቦታ የተያዘ ወይም በግዥ የተገኘ አዲስ ሁብረ-ንብ

6) To ensure that the honeybee colony is free from disease, a honeybee colony obtained through reproductive swarming

ከበሽታ ነፃ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ እንዲቻል ለ14 ቀናት ከነባር ሀብረ ንቦች ጋር መቀላቀል የለባቸውም፡፡

or a newly purchased one shall not be mixed with the existing colony before 14 days

## ክፍል ስድስት

## Part Six

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና የመዝገብ አያያዝ

## Issuance of Certificate of Competency Assurance and Record-Keeping

### 18. የብቃት ማረጋገጫ ስለመስጠት

### 18. Issuance of Certificate of Competency Assurance

1) ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 እና 20 ስርየተጠቀሱትን መስፈርቶች በማሟላትና በዕዝል 01 ስር የተመለከተውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለተቆጣጣሪው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

1) Any person shall acquire a certificate of competency assurance by meeting the requirements set out in Articles 19 and 20 of this Directive and fill in and submit the application form provided in Annex 01 to the regulatory body;

2) የድርጅቱ ዝግጅትና ማመልከቻ የተሟላ ሲሆን ከተቆጣጣሪው አካል የተውጣጡ ሶስት አባላት ያሉት ባለሙያዎች በመላክ እንዲታይለት ይደረጋል፡፡

2) When the organization fulfils the criteria and the application, the regulatory body shall send three relevant members of experts to make the supervision.

3) አስፈላጊውን መስፈርት ስለመሟላቱ የተቆጣጣሪው አካል ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሟላታቸውን በመፈተሽና በማረጋገጥ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

3) The experts from the regulatory body shall submit report by checking and verifying the compliance of requirements set out in this Directive.

4) ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በተቆጣጣሪው አካል ከተረጋገጠ በኋላ የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻውን ካስገባበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 የስራ ቀናት ውስጥ ይሰጠዋል፡፡

4) The regulatory body shall issue a Certificate of competency assurance within 15 working days from the date of filing of the application after verifying that the organization fulfils the necessary criteria.

5) ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ካላሟላ መስፈርቶቹን እንዲያሟላ በጽሑፍ ይገለፅለታል፡፡

5) If the organization does not meet the required criteria, it will be notified in writing to meet the requirements.

| | |
|---|---|
| 6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 5 መስፈርቶችን እንዲያሟላ በጽሑፍ የተገለፀለት ድርጅት መስፈርቶቹን ማሟላቱን በባለሙያዎች ሪፖርት ቀርቦ ከተረጋገጠ በኋላ ከ10-15 ባሉት የስራ ቀናት የብቃት ማረጋገጫው ይሰጠዋል። | 6) A certificate of competency assurance shall be issued to the organization that is notified in writing to fulfil criteria under sub-article 5 of this article, within 10-15 working days after a report has been submitted and verified by the experts of the regulatory body. |
| 7) በዚህ አንቀጽ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው በመስፈርቱ መሰረት እየሰራ ስለመሆኑ በየዓመቱ በተቆጣጣሪው አካል ኦዲት ይደረጋል። | 7) According to this article, the person who has been granted the certificate of competence is audited annually by the regulatory body to verify that they are working in accordance with the standards. |
| **<u>19. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መሰረታዊ መስፈርቶች</u>** | **<u>19. Basic Requirements for Obtaining a Certificate of Competency Assurance</u>** |
| 1) ማንኛውም ሰው ለንግድ በንብ ልማት ብቃት ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት። | 1) Any person shall meet the following requirements to acquire a certificate of competence assurance for commercial beekeeping development: |
| ሀ. ከልማቱ ስለሚመረተው የንብ ውጤቶች የንግድ አዋጭነት ዕቅድ ማዘጋጀትና ማቅረብ፤ | a) Develop and present a business plan on bee products produced from the development; |
| ለ. የማልሚያ ቦታው የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ፤ | b) Provide title dead or lease agreement for the development site. |
| ሐ. በልማቱ መስክ አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ወይም አግባብነት ያለው ባለሙያ መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤ | c) Provide evidence of appropriate educational preparation and skills in the field of development or provide evidence of employment of the appropriate professional; |
| መ. የንግድ አዋጭነት ዕቅድ መሠረተ ልማቱን ለማካሄድ በቂ ካፒታል ያለው ስለመሆኑ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤ | d) Provide banking evidence showing sufficient capital for the development in accordance with the business plan. |
| ሠ. እንዲያገግሙ በተከለሉ ቦታዎች፤ በማህበራት ደን፤ ፓርኮችና ጥብቅ ቦታዎች | e) Must submit a written work permit from the relevant body in order to develop in areas reserved for recovery, |

| | |
|---|---|
| ላይ የሚያንብ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የጽሑፍ ስራ ፈቃድ ማቅረብ፤ | forest of associations, parks, and protected areas. |
| 2) ማንኛውም ሰው ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጥ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት። | 2) Any person shall meet the following requirements to acquire competence assurance to establish a commercial queen bee rearing station or center: |
| ሀ. ንግስት ንብን በማባዛት ስለሚገኘው ውጤት የንግድ አዋጭነት ዕቅድ ማዘጋጀትና ማቅረብ፤ | a) Provide a business plan for queen bee rearing |
| ለ. የማልሚያ ቦታው የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ፣ | b) Provide a title deed or lease agreement for the development site; |
| ሐ. በልማቱ መስክ አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ወይም አግባብነት ያለው ባለሙያ መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤ | c) Provide evidence of appropriate educational preparation and skills in the field of development or provide evidence of employment of the appropriate professional; |
| መ. የንግድ አዋጭነት ዕቅድ መሠረት ልማቱን ለማካሄድ በቂ ካፒታል ስለመኖሩ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤ | d) Provide banking evidence showing sufficient capital for the development in accordance with the business plan. |
| ሠ. እንዲያገግሙ በተከለሉ ቦታዎች፤ በማህበራት ደን፤ ፓርኮችና ጥብቅ ቦታዎች ላይ የሚያንብ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ ማቅረብ፤ | e) Must submit a written work permit from the relevant body in order to develop in areas reserved for recovery, forest of associations, parks, and protected areas. |
| 3) ማንኛውም ሰው የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት። | 3) Any person shall meet the following requirements to acquire competency assurance for the establishment of beekeeping equipment and material production enterprise፡ |
| ሀ. የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረት ሥራ በመለየት የንግድ አዋጭነት ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ፤ | a) Prepare a business plan for beekeeping equipment and materials production |

| | |
|---|---|
| ለ. የመሸጫ ቦታ እና መጋዘን የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ፣ | b) Provides Proof of title dead or lease agreement for sale place and warehouse |
| ሐ. የመሸጫ ቦታ እና መጋዘኑ ከተለያዩ ኬሚካሎች፣ ኬሚካላዊ ይዘትና የመትነን ባህሪይ ያላቸው ምርቶች ከሚመረቱበት ፋብሪካዎች አካባቢ ቢያንስ 50 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፤ | c) The place of sale and warehouse should be 50 meters away from the factory with various chemicals and products that have chemical content and evaporating behaviour |
| መ. በንግድ አዋጭነት ዕቅዱ መሠረት ለሥራው ማከናወኛ በቂ ካፒታል ስለመኖሩ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤ | d) Provide banking evidence of sufficient capital for the operation in accordance with the business plan |
| 4) ማንኛውም ሰው የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤ | **4)** Any person shall meet the following requirements to acquire a Certificate of competency assurance for the establishment of a bee product processing and packaging company: |
| ሀ. ለማቀነባበርና ለማሸግ የተፈለገውን የንብ ውጤት/ቶች በመለየት የንግድ አዋጭነት ዕቅድ ማዘጋጀት፤ | a) Develop a business plan on desired bee products to process and packing |
| ለ. ለማቀነባበርና ለማሸግ ሥራ የሚያስፈልግ ግንባታ ለማካሄድ ኬሚካላዊ ይዘትና የመትነን ባህሪይ ያላቸው ምርቶች ከሚመረቱበት ፋብሪካዎች አካባቢ ቢያንስ 50 ሜትር የራቀና አቧራና ብናኝ የሌለበት ቦታ ማዘጋጀት፤ | **b)** Construction site for bee product processing and packaging should be 50 meters away from the factory with various chemicals and products that have chemical content and evaporating behaviour. |
| ሐ. የግንባታ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ፣ | c) Provide title dead or lease agreement for Processing and packaging site. |
| መ. በንግድ አዋጭነት ዕቅዱ መሠረት ለሥራው ማከናወኛ በቂ ካፒታል ስለመኖሩ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤ | d) Provide banking evidence of sufficient capital for the operation in accordance with the business plan |

| | |
|---|---|
| ሠ. በመስኩ አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ወይም አግባብነት ያለው ባለሙያ መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤ማሟላት አለበት፡፡ | e) Provide evidence of relevant educational preparation and skills in the field of processing and packaging or provide proof of employment of the appropriate professional; |
| ረ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡ | f) Must meet all the requirements set out in Article 13 of this Directive. |
| 20. <u>የግዴታ ወረቀት የሚፈረምባቸው ሁኔታዎች</u> | **<u>20. Requirements for Signing a Mandatory Paper</u>** |
| 1) ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት እና በንግድ ንግስት ንብ ርቢ መሰማራት የሚፈልግ ሰው፡- | 1) Any person who wants to engage in commercial beekeeping and commercial queen bee rearing Shall have the following obligations: |
| ሀ. ሕይወት ያላቸው ንቦች፣ ያገለገሉ ቀፎዎች፣ የንብ መገልገያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ከውጪ ገዝቶ ላለማስገባት፤ | a) Avoid importing live bees, used hive beekeeping equipment, and materials. |
| ለ. ማንኛውንም ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ የንብ ውጤቶች በጥራትና ደህንነት እንዲመረቱ የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጠብቆ ለመስራት፤ | b) To work in compliance with any proclamations, regulations, and directives issued for the protection of natural resources, and for the production of bee products with quality and safety. |
| ሐ. የተቆጣጣሪው ባለስልጣን ኢንስፔክተር ማንኛውንም ዓይነት ኢንስፔክሽን ለማካሄድ በሚቀርብበት ጊዜ ፈቃደኛ የመሆን ፤ | c) To be willing when the inspector of the concerned regulatory body approaches to conduct any inspection. |
| መ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶች አደራጅቶ መያዝ፣ የምርቱን የሥርጭት አውታር መረጃ መያዝና ለምርመራና ክትትል አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከታቸው አካላት ግልጽ የማድረግ፣ ግዴታ አለበት፡፡ | d) Organizing complete work records and documents, keeping the information of the product's distribution network, and making it clear to the relevant legal bodies when it is necessary for inspection and monitoring. |
| 2) ማንኛውም የማናቢያ መሳሪያዎችና | 2) Any person who wants to establish a Beekeeping equipment and material |

| | |
|---|---|
| ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት ማቋቋም የሚፈልግ ሰው፡- | production enterprise shall have the following obligations: - |
| ሀ. ጥራትና ደረጃውን በጠበቀ የንብ ቀፎ ጥሬ ዕቃ፣መሣሪያና ቁሳቁስ የማምረት፣ | a) Produce quality and standard beehives, raw materials, equipment, and materials; |
| ለ. ተቆጣጣሪውአካልስለማሽኖች፣መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች እና የምርት ጥራትና ክምችት ፍተሻ ለማድረግ በሚጠይቅበት ጊዜ የመተባበር፣ | b) To cooperate when the regulatory body requests to carry out inspections of machinery, equipment and materials and product quality and inventory; |
| ሐ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶች አደራጅቶ መያዝ፣ የምርቱን የሥርጭት አውታር መረጃ መያዝና ለምርመራና ክትትል አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለተቆጣጣሪው አካል ግልጽ የማድረግ፣ግዴታ አለበት ፡፡ | c) Organize a complete work record a documentation, describe the distributi network of the product, and make it clear the relevant regulatory body when necessa for inspection and monitoring. |
| 3) ማንኛውም የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ማቋቋም የሚፈልግ ሰው፡- | 3) Any person who wants to establish a Honeybee Product Processing and Packaging enterprise shall have the following obligations: - |
| ሀ. የንብ ውጤቶችን ምንጭ፣ ዓይነትና ጥራት ለይቶ ማቀነባበርና ማሸግ እንዲሁም የጥራት ደረጃና ደኅንነት ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ገበያ የማይመጥን ሆኖ ሲገኝ ከምንጩን መለየት፣ ማሻሻልና ዳግም እንዳይከሰት የመከታተልና የማረም ግዴታ፤ | a) Identify the source, type, and quality of bee products, process and package them, and when the quality level and safety are not suitable for the domestic or foreign market, identify the problem from the source, improve it, and monitor and correct it so that it does not happen again; |
| ለ. ማንኛውንም ስለንብ ውጤቶች ጥራትና ደኅንነት የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጠብቆ የመሥራት፤ | b) To work in compliance with any proclamations, regulations, and directives issued for the quality and safety of bee products; |
| ሐ. ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥርና የፍተሻ ስራ እንዲያካሂድና የንብ ውጤቱን የሚያሰባስብበትን አካባቢ የማስፈተሽ፣ ግዴታ አለበት፡፡ | c) The regulatory body shall carry out the control and inspection work and to inspect the area where the bee product is collected. |

**21.ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለመስጠት**

ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲበላሽበት ወይም ሲጠፋበት ወይም ሲወድምበት ምትክ ሊያገኝ የሚችለው፡-

1) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ከሆነ ከነብልሹቱ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስና ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤

2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ወይም ከወደመበት ስለመጥፋቱ ወይም ስለመውደሙ የሚገልጽ ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤

**21. Issuance of Replacement competency assurance Certification**

Any person shall obtain replacement when the previous certificate of competency assurance is damaged or lost or destroyed where:

1) If the certificate of competency assurance is damaged, he shall return the damaged certificate and ask for a replacement.

2) If a certificate of competency assurance has been lost or destroyed, when he submits proof of the loss or destruction from the relevant body and requests a replacement.

**22. የመዝገብ አያያዝ**

ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት፡-

1) ለሚያመርታቸው የንብ ውጤቶች፣ ለሚያባዛቸው ንቦች፣ ለሚያስመጣቸውና ለሚያከፋፍላቸው ጥሬ እቃዎች ወይም ግብአቶች ምንጭና ስለሚሸጣቸው የንብ ውጤቶች መነሻ ዝርዝር መረጃ ለይቶ የመያዝ፤

2) ስለአመረተው ወይም ስላስመጣው፣ስለአከፋፈለው፣ ስለላከው፣ ስለተበላሸው፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ስላለፈበት ሌሎችም ከንብ አያያዝ ጋር ተያያዥነት

**22. Record Keeping**

Any business for commercial beekeeping Development, for a commercial queen beekeeping station or center; beekeeping equipment and material production enterprise, Honeybee product Processing and Packing Company shall:

1) Keep detailed information about A source for bee products produced by beekeeping companies, bees that reproduce, import, and distribute raw materials or inputs; Origin of bee products for sale

2) When required by the regulatory body or appropriate body, properly handle and produce documents related to produced it for import, distribution, export, spoilage,

ያላቸውን ሰነዶች በአግባቡ የመያዝና በተቆጣጣሪው አካል ወይም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የማሳየት፣

3) የንብ ውጤቶችን ወይም ግብአቶችን የገዛበትና የሸጠላቸውን ድርጅቶች ስምና ሙሉ አድራሻ በዝርዝር መያዝ፣

4) ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ወቅታዊ የማድረግ፣በአግባቡ የመያዝና ለተቆጣጣሪው አካል ወይም አግባብ ላለው አካል ግልጽ ማድረግ፤ አለበት።

## ክፍል ሰባት

## አስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድ

### 23. ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሚያሳግድ፣ ከሚያሰርዝ ወይም ሌሎች ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ከሚያስወስድ ጥፋት ውጪ ያሉ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን መተላለፍ፣ በተቆጣጣሪው አካል እንደአግባቡ የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥባቸው ይችላል።

2) አናቢው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 5 የተጠቀሱትን ግዴታዎች ተግባራዊ ሳያደርግ ቢገኝና የሚያጓጉዛቸው ህብረ ንቦች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በተላይ ተላላፊ በሆኑ በሽታዎችና ተባዮች የተጠቁ መሆናቸው የተረጋገጠ ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት፦

ሀ.ህብረ-ንቦቹን ወደ ቀድሞው ቦታ በመመለስ አስፈላጊው ህክምናና እንክብካቤ በአናቢው ወጪ እንዲሸፈን ይደረጋል፤

ለ. ህብረ-ንቦቹ በበሽታ ወይም በተባይ የተጠቁበት ደረጃ በባለሙያ ከታየ በኋላ

expiration date, and other bee handling requirements related to beekeeping;

3) Provide the names and full addresses tof the companies that have purchased and sold bee products or inputs.

4) The above-mentioned information should be updated, kept properly, and made clear for the regulatory authority or appropriate body

## Part Seven

## Administrative Measures

### 23. Warning

1) The regulatory body shall give a verbal or written warning as a case may be, for violation of provisions of this directive other than an offense that entails suspension or cancellation of certificate of competency, or other severe administrative measures.

2) If a beekeeper fails to comply with the obligation referred to in sub-articles 3 to 5 of article17 of this Directive; and is verified that the bee colony he moves is completely or partially infected with infectious diseases and pests, he shall be given a written warning and፡

a) Shall return the bee colony to the previous place And cover expenses of necessary treatment And care;

b) Dispose of infected bee colonies if they do not improve or recover after being diagnosed with a disease or pest by

የማይሻላቸው ወይም የማያገግሙ ከሆነ በአናቢው እንዲወገዱ ይደረጋል፤ ሆኖም ግን አናቢው ማስወገድ ካልቻለ በተቆጣጣሪው አካል እንዲወገድ ተደርጎ ወጪው አናቢው እንዲሸፍን ይደረጋል፤

ሐ.በተቆጣጣሪ አካል ማረጋገጫ ሳያገኝ አናቢው በሚያሏዙራቸውና በሌሎች ሀብረ- ንቦች ወይም በሰዎችም ሆነ በእንስሳት ላይ የበሽታ፣ የተባዮችና ሌላ ማናቸውም ዓይነት ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ወይም ካስከተለ በወንጀል ህጉ ተጠያቂነት አግባብ ባለው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

a professional; but if the beekeeper fails to do so, the regulatory body shall remove them at the expense of the beekeeper;

c) If the beekeeper is found to be causing disease, pests, or any other damage to the bees, humans, or animals failing confirmation from the regulatory body, he shall be liable according to the provisions of the relevant civil law in addition to criminal liability.

### 24. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳ

ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣ የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በተቆጣጣሪው አካል ጉድለቶቹ እስኪስተካከሉ ድረስ ለዘመኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እስከ ሶስት ወራት ለሚደርስ ጊዜያት ሊያግድ ይችላል።

1) ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ከሶስት ወር በፊት ሳያሳውቅ የድርጅቱን የቦታና የአድራሻ ለውጥ ካደረገ፤

2) ተቆጣጣሪው ባለስልጣን በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው የቁጥጥር

### 24. Suspension of Certificate of Compete assurance

If any commercial beekeepin Development, for a commercial queei beekeeping station or center; beekeepin equipment and material productio enterprise; Honeybee product Processin and Packing Company is found liable fo any of the following reasons, the regulator body shall suspend the certificate o competency assurance for not more tha three months, until the deficiencies ar corrected.

1) If he changes the place and address of his company without notifying the regulatory body three months in advance;

2) If he obstructs any of the inspections conducted by the regulatory body in his establishment;

| | |
|---|---|
| ስራዎች እንዲያከናውን ለመተባበር ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ካሰናከለ፤ | |
| 3) ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ድርጅቱን የማያስተካክል ከሆነ ወይም መመሪያው ባስቀመጠው መሰረት ተግባሩን ካልፈጸመ፤ | 3) If he fails to correct according to the warning notice given by the regulatory body more than twice or comply with this directive. |
| **<u>25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ</u>** | **<u>25. Revocation of Certificate of Competency assurance</u>** |
| ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፤ የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ተቆጣጣሪው አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡- | If any commercial beekeeping Development, for a commercial queen beekeeping station or center; Beekeeping equipment and material production enterprise; Honeybee product Processing and Packing Company, or Honey bee product marketing enterprise is found liable for any of the following reasons, the regulatory body may revoke his certificate of competency assurance. |
| 1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ መመሪያው ከሚፈቅደው አሰራር ውጭ በሆነ መንገድ የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፤ | 1) If it is found that the certificate of competency assurance is obtained in a way that is not in accordance with this directive; |
| 2) በማናቸውም መንገድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለሌላ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ፤ | 2) If it is found that he has transferred the certificate of competency assurance to another party; |
| 3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ከወጣበት ዓላማ ውጭ ሲሰራ ከተገኘ፤ | 3) If it is found to be operating contrary to the purpose for which the certificate of competency assurance was issued; |
| 4) ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ጽሁፍ የሌለው፣ የንብ ውጤቶችን የከለሰ፣ አስመስሎ ያቀረበ፣ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የማናቢያ ቁሳቁሶችና የንብ ውጤቶች ለገበያ ያቀረበ ወይም በማናቸውም ሁኔታ በህገወጥ ንግድ ውስጥ | 4) does not have labelling on the product, adulterated or supplied another product which is not a bee product, supplied substandard equipment and bee products, has entered into the trade illegally; |

ገብቶ የተገኘ፤

5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በወቅቱ ያላሳደሰ እንደሆን፤

5) If the certificate of competency assurance is not renewed on time;

6) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 24 መሰረት እገዳ ተጥሎበት ጉድለቶቹን ያላስተካከለ እንደሆን፤

6) Fails to correct deficiency up on its suspension according to article 24.

**26. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ስለመመለስ**

**26. Return of Certificate of Competency assurance to the Regulatory body**

1) ማንኛውም ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፤ የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፤ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት አይነትና የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ ነባሩን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለተቆጣጣሪው አካል ወዲያዉኑ መመለስ አለበት፡፡

1) Any commercial beekeeping Development, for a commercial queen beekeeping station or center; beekeeping equipment and material production enterprise; Honeybee Product Processing and Packing Company shall return his old certificate of competency assurance When the owner corrects mistakes that let for rejection of the certificate and his application for a new certificate of competency assurance is accepted by the regulatory body.

2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ፤ በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ የንግድ ስራውን ካቋረጠ ድርጅቱ ነባሩን ፈቃድ በአንድ ወር ጊዜ የስራ ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን መመለስ አለበት፡፡

2) If the certificate of competency assurance is revoked, has not been renewed within the specified renewal period, or the business is terminated voluntarily, the person shall return the existing certificate to the regulatory body within one month working days.

**27. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳ ስለማንሳትና የተሰረዘውን ስለመተካት**

**27. Lifting of Suspended and Replacement of Revoked Certificate of Competency assurance**

1) ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የታገደበት በንግድ ንብ ልማት፤ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፤የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ

1) Any certificate of competency suspended for commercial beekeeping Development, for a commercial queen

ማምረቻ ድርጅት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት የተጣለበት እገዳ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ጥፋቱን አምኖ ሲያስተካክል በባለስልጣኑ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

beekeeping station or center; beekeeping equipment and material production enterprise; Honeybee product Processing and Packing Company will be lifted if the complaint is submitted and accepted in accordance with this directive or if the organization admits and corrects his error.

2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ማንኛውም ድርጅት በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝና ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት ሙሉ ለሙሉ በማረምና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ የተደረገው ማስተካከያ በባለስልጣኑ በባለሙያዎች ተረጋግጦ በተሰረዘው የምስክር ወረቀት ምትክ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

2) Any company whose certificate of competency assurance has been revoked shall be replaced if the complaint is submitted and accepted in accordance with this directive and is verified by experts that the organization admits and fully corrects the breach.

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part Eight
## Miscellanies Provisions

### 28. ግንዛቤ ስለመፍጠር

ይህን መመሪያ የሚያስፈጽሙ አካላት በዚህ መመሪያ ላይ ስለተመለከቱ ጉዳዮች የምክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስጠት አለባቸው፡፡

### 28. Creating awareness

The executive bodies for this directive shall provide advice and conduct awareness creation regarding issues covered under this directive.

### 29. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ

### 29. Inapplicable Directives

Any directive and practice that is inconsistent with this directive shall not apply to matters covered under this

ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 30. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበና በተቋሙ ድህረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

መስከረም/2017 ዓ/ም አዲስ አበባ

ዶ/ር ግርማ አመንቴ

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር

directive.

## 30. Effective date

This directive is approved by the Ministry of Agriculture and shall enter into force upon the date of its registration with the Ministry of Justice

October, 2024 Addis Ababa

Girma Amente (PhD),

Minister of the Ministry of Agriculture

**ዕዝል 01**

የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ማመልከቻ ቅጽ 01

ቁጥር:---------------------------

ቀን:-----------------------

ለኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን

ለ------------------------------------------ ዴስክ/መሪ ስራ አስፈፃሚ

<u>አዲ ስአበባ</u>

ጉዳዩ፡ የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ለማቅረብ

የአመልካች ግለሰብ/ተቋም/ ድርጅት ስም ----------------------------የንግድ ስም ------------------------------------------------------------------------------

የንግድ/ድርጅት/ተቋም አድራሻ፡
ክልል ------------------------------ ክ/ከተማ ----------------------------ወረዳ---------------------
የቤት ቁጥር ----------------
የድርጅት ምዝገባ ቁጥር--------------የንግድ ፈቃድ ቁጥር----------የስልክ ቁጥር፡ ሞባይል ------------------------ የቢሮ -----------
በአዋጅ ቁጥር 980/2008 በተደነገጉት ሁኔታዎች ላይ በመመሥረት የግብርና ሚ/ር በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት ባዘጋጃቸው የንግድ ሥራ መደቦች ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ መሠረት የ------------------------------------------------------------------------- ሥራ ለማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

በግልጽ የሚነበብ የድርጅቱ ማህተም ፊርማ
ሥራ አስኪያጅ (ተወካይ)

**Appendix 01**

Competency assurance Application Form 01

Ref. Number ------------------------------

Date-------------------------------

Ethiopian agriculture authority

-----------------------------------------

Desk/lead executive

<u>Addis Ababa</u>

Subject: - request for competency assurance

Name of applicant / institution / organization ------------------------------------------- ------------------ Business Name ----------------------------------------------------------------------------------------------- Business / Organization / Institution Address

Region ------------------------------ Sub City ------------------ ---------------

---------------- District ---------------------
Home Number ----------------Enterprise Registration Number -----------------
Business License Number --------------------
Telephone number die mobile ---------------- --------- Office --------------------------
Pursuant to the conditions set out in Proclamation No. 980/2016, in accordance with the Competency Assurance directive issued by the Ministry of Agriculture for the qualification of business positions in the sector. Of ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------ ---- I ask for it.

Best regard,

Clearly visible seal of the organization signature
Manager (Representative)

ዕዝል 02

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጽ 02

ቁጥር: ---------------------------

ቀን: --------------------------

ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

<u>አ ዲስ  አበ ባ</u>

ጉዳዩ፡ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

------------------------------------------------------------

--------------

የተባለግ/ል/ኃ/የተ/የግ/ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 980/2008

በተደነገገውና ሚኒስቴር መ/ቤታችን በ------------------ ዓ.ም ባወጣው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መሠረት፣ለ------------------------------------------------------------------------------------

ሥራ የፈቃድ መስጫ መደብ ቁጥር ------------------------------ ላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች:

Appendix 02

**Competency assurance Certificate Form 02**

**Ref. Number** --------------------------------

**Date**---------------------------------

**Ministry of Trade and regional integration**

**<u>Addis Ababa</u>**

**Subject: competency assurance certificate**

We certify -----------------------------------------------------------------------------------

Private PLC as prescribed inProclamation No. 980/2016 and the criteria of competency assurance set by our ministry at --------year, for --------------------------------------------------------------------------------------------------------------

Work Licensing Category Number, ------------------------Since it is a qualified institution, we confirm that this certificate of competency assurance has been issued that fulfilled criteria's set as follows:-

1 -------------------------------------------------------

----------------------

2 -------------------------------------------------------

----------------------

3 -------------------------------------------------------

----------------------

4 -------------------------------------------------------

----------------------

5 -------------------------------------------------------

------------------------አሟልቶ የተገኘ ተቋም ስለሆነ ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን እናረጋግጣለን።

ከሰላምታ ጋር

1 -------------------------------------------------------

----------------------

2 -------------------------------------------------------

----------------------

3 -------------------------------------------------------

----------------------

4 -------------------------------------------------------

----------------------

5 -------------------------------------------------------

----------------------

Best regard